# እጃችንን እናውጣ

**ቶሎሳ ኡርጌሳ 03-12-18**

በርዕሴ ላይ 'እጃችንን እናውጣ' ያልኩት ያለ ምክንያት አይደለም። እጃችንን የምናወጣው፤ ለእኩይ ምግባር አይደለም። እጃችንን የምናወጣው፤ ለማናምንበትና ጥቅማችንን ለሚፃረር ነገር አይደለም። እጃችንን የምናወጣው፤ ዓላማ ቢስና ረብ የለሽ ለሆነ ነገር አይደለም። እጃችንን የምናወጣው፤ በሀገራችን ላይ ተንኮልን ሸብበው ጧት ከቤታችን ወጥተን ማታ ተመልሰን እንዳንገባ 'የቀበሮ ባህታዊ' በመሆን ጉድጓድ ለሚቆፍሩልን ሴረኞች አይደለም። ወደ ትናንት አሳዛኝና አሳፋሪ ማንነታች ተመልሰን እንድንደፈቅም አይደለም። እጃችንን የምናወጣው፤ ለውጭ ሃይሎች በማደጎ ልጅነት ገንዘብ እየተቀበሉ ሀገራቸውን ለባዕዳን ለሚሸጡ "ይሁዳዎች" እንዲሁም ለዘመናት ይዘናቸው የመጣናቸውን አኩሪ እሴቶቻችንን ለሚሸረሽሩብንና በማንነት ላይ የተመሰረተ የብሔር ጥቃት ለሚፈፅሙብን ተላላኪዎች አይደለም። ለቀለም አብዮት ምንደኞችም አይደለም።

አዎ! እጃችንን የምናወጣው፤ ተጠቃሚነታችንን ለሚያጎላ ሰናይ ጉዳይ ነው። እጃችንን የምናወጣው፤ ለሰላምና ስለ ሰላም ብቻ ለሚከናወኑ ክስተቶች ነው። ሰላም የሁሉም ሀገራዊ ጉዳዮች መሰረት ስለሆነ ነው 'እጃችንን እናውጣ' ማለቴ። ያለ ሰላም ፈጣንና ተከታታይ ልማትን እንዲሁም ስር እንዲሰድ የሚፈለግ የዴሞክራሲ ባህል ግንባታን ማሰብና መተግበር ስለማይቻል ነው እጃችንን እንድናወጣ የሻትኩት። ሰላም በሌለበት ሁኔታ፤ ስለ እነዚህ ጉዳዩች ማውሳት ከጉንጭ አልፋነት የማይዘል አሊያም ላም ሳይኖር ኩበት የመልቅም ያህል ስለሚሆን ነው— እጃችንን ማውጣት እንዳለብን የምናገረው።

ርግጥ ሰላምን የማይፈልግ ህዝብ የለም። የየትኛውም ሀገር ህዝብ ሰላምን አጥብቆ መሻቱ የግድ ነው። ሰላምና መረጋጋቱ ከተስተጓጎለ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው አደጋ ላይ መውደቁ እንደማይቀር ስለሚገነዘብ ሰላምን እንደ ስስት ቢመለከት ብዙም የሚደንቅ አይመስለኝም። ምክንያቱም የሰላም አለመኖር እንደ ሀገርም ይሁን እንደ ግለሰብ የሚያስከትለው አደጋ ግልፅ ስለሆነ ነው። እናም ሁሉም ህዝብ ስለ ሰላም ሲል እጁን ማውጣቱ የግድ ነው።

ጉዳዩን ወደ እኛ ሀገር ስንመልሰውም፤ የሀገራችን ምጣኔ ሃብት እያደገና እየተመነደገ እንዲሁም የህዝቡ የኑሮ ሁኔታ በልማቱ ላይ ባለው ተሳትፎ መጠን እየጎለበተ ብሎም ገና ጮርቃ የሆነው የዴሞክራሲ

ስርዓት ግንባታ ሂደታችን ተደናቅፎ ወደ ቀደምት ፊውዳላዊና አምባገነናዊ ስርዓቶች መመለስ የሚፈልግ ህዝብ የለም። ሰላም ለኢትዮጵያ ህዝብ ዋጋው ምን ያህል እንደሆነ ግልፅ ነው። ከኢትዮጵያ ህዝብ በላይ ለሰላም እጁን የሚያወጣ ከቶም ከየትም ሊገኝ ይችላል ብዬ አላስብም።

የሀገራችን ህዝብ ትናንት በሰላም እጦት ሳቢያ በድህነት ውስጥ ሲዳክር የነበረ ነው። ላለፉት 27 ዓመታትም ከሰላም የሚገኙ ትሩፋቶችን ሲያጣጥም አሁን የሚገኝበት ደረጃ ደርሷል። እናም ሲያጣጥመው የመጣው ሰላም በአንዳንድ የውስጥና የውጭ ሃይሎች እንዲሁም የሀገር ውስጥ ጉዳይ ፈፃሚዎቻቸው አማካኝነት ተሰናክሎ የኋሊት ጉዞ ማከናወን አይፈልግም። ለዚህም ነው— በየመገናኛ ብዙሃኑ ስለ ሰላም አስፈላጊነት እጁን እያወጣ ጮክ ብሎ ሲናገር የምናደምጠው። ይህም በእኛ ሀገር ውስጥ ሰላምን የማስተጓጎል ተግባር ጥቂት የራሳቸው ፍላጎት ያላቸው የስልጣን ጥመኞች ፍላጎት እንጂ፣ ህልቆ መሳፍርት የሆነውን በርካታ ሰላም ወዳጁን የሀገራችንን ህዝብ የሚወክል አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

እነዚህ ሁከት አምላኪ ሃይሎች የሀገራችን ፖለቲካል-ኢኮኖሚ አውድ (Political-Economy Context) የሚፈቅዳቸው አይደሉም። የሀገራችን አውድ በፖለቲካው ረገድ ዴሞክራሲያዊና የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አክብሮ የሚያስከብር በህገ መንግስታዊ ስርዓት እውን የሆነ ነው። በምጣኔ ሃብቱም በኩል፣ የዜጎችን ተጠቃሚነት በልማቱ ላይ ባላቸው ተሳትፎ ልክ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አውድ ነው።

የሁከት አምላኪዎቹ አውድ፣ 'ከዚህ የተለየ ነው' ተብሎ ብቻ የሚገለፅ አይደለም። ጉዳዩ "አራምባና ቆቦ" እንዲሉት ዓይነት ከሀገራችን ተጨባጭ አውድ እጅግ ያፈነገጠ ነው። ይህ አውድ በፀረ-ዴሞክራሲያዊነት መርህ የሚመራና ይህንንም ለማስፈፀም ማናቸውንም የህዝብ ጥያቄዎች ቀምቶ የራስ በማድረግ በኃይል ለማስፈፅም የሚሞክር ነው። አውዱ በዜጎች ማንነት ላይ ተመስርቶ ጥቃት ይፈፅማል፣ ዜጎች በሰላም ገብተው እንዳይወጡ ድንጋይ ቀልሎ መንገድ ይዘጋል። የሀገር ኢኮኖሚን ለመጉዳት በማሰብ ዜጎች ከቤታቸው እንዳይወጡ በማስፈራራት መደበኛ እንቅስቃሴን ያስቆማል። አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሌሎች ሀገር ውስጥ ቢሆን እጅግ ከባድ ቅጣት በሚያስከትለው ፀጥታ ኃይሎችን እስከ ማጥቃትና ለሰላም ማስከበሪያ የተሰጣቸውን መሳሪያ እስከ መቀማት የደረሰ ተግባር ይፈፅማል። የውጭ ተላላኪ በመሆንም ገንዘብ እየተቀበለ በጎዳና ላይ ነውጥ የቀለም አብዮትን ለማስፈፀም ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለመናድ ማናቸውንም ተግባሮች የሚከውን ተላላኪ አውድ ነው። አንድ ዜጋ 'የእገሌ ብሔር አባል ነው' በማለት ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ ክብሩን እንዲሁም በሀገሩ ተዘዋውሮ የመስራት

መብቱን ይነፍጋል። በፍትሐዊ ተጠቃሚነት ሰርቶ ራሱን መለወጥ ሳይሆን፤ ሌላውን በመቀማት የዘረፋ ተግባር ተሰማርቶ ህይወቱን ለመቀየር ይፈልጋል፤ ይተገብራል።…ሌላ ሌላም ያደርጋል።…

ይህ የሁከትና የብጥብጥ እንዲሁም የዘመናት እሴቶቻችንን በኃይል የሚሸረሽር አውድ የሀገራችን ሰላም አዋኪ መሆኑን ተመልክተናል። በዚህኛውም ላይ የሰላም ፈላጊነታችንን እጅ ማውጣት ይኖርብናል። 'ሰላማችንን አታውክ!' ብለንም እጃችንን ልናወጣበት ይገባል። ከፍ ሲልም፤ የአውዱን ፈፃሚዎች በማጋለጥና ህግ ፊት እንዲቀርቡ በማድረግም የጥቆማ እጃችንን ልናወጣባቸው ይገባል።

ርግጥ ነው—ኢትዮጵያ ባለፉት 27 ዓመታት የሰላም ተምሳሌት ተብላ ስትጠቀስ ኖራለች። ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት በማስመዝገቧና የነገ ራዕይዋ ከወዲሁ እየታየም ነው። 'ትልቅ ነበርን፣ ትልቅም እንሆናለን' ብላ ተነስታለች። ሰላማችን አስተማማኝ በመሆኑ የተለያዩ የውጭ ኩባንያዎች መዋዕለ ነዋያቸውን በማፍሰስ በልማቱ መስክ አብረውን እየሰሩ ነው።

ምንም እንኳን ሰላማችን ባለፉት ዓመታት ህዝባዊ መሰረት ባለው ጥሩ መሰረት ላይ የተገነባ በመሆኑ፤ እንደ ደቡሽት ቤት በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሊፈርስ ባይችልም፤ የተረጋጋና አስተማማኝ ሰላም ያላቸው ሀገራት ሰላማቸው በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሲደፈርስ ብሎም በትርምስና ሁከት ውስጥ ሲቆዩ የተመለከትናቸው አጋጣሚዎች ጥቂት አይደሉም። በእስላማዊ መንግስት (IS) የሚታመሱት ሶሪያና ኢራቅ፣ በታሊባን ሙጃሂዲኖች ቁም ስቅሏን የምታየው አፍጋኒስታን፣ በሺሃና ሱኒ ሙስሊሞች እሰጥ አገባ የውጭ ኃይሎች የእጅ አዙር ውጊያ አውድማ የሆነችው የመን እንዲሁም በእርስ በእርስ ግጭት ሳቢያ ፍዳዋን እያየች የምትገኘው ለጋዋ ሀገር ጎረቤታችን ደቡብ ሱዳን በዚህ ረገድ ከብዙ በጥቂቱ ተጠቃሾች ይመስሉኛል።

የሀገራችን ፖለቲካል-ኢኮኖሚ አውድ ራሱን በራሱ የሚያርምበት አሰራር ያለው በመሆኑ በምሳሌነት እንዳቀረብኳቸው ዓይነት ሀገራት መሆናችን አይቀርም ብዬ ባስብም፤ የሁከትና የብጥብጥ አውደኞች ግን የሚፈልጉት ሰርክ በእነርሱ አጀንዳ ተውጠን ከድህነት ለመውጣት የምናደርገውን ጥረት እንዲኮላሽ ማድረግ መሆኑ ግልፅ ነው። ታዲያ ይህ ህገ መንግስቱን የሚፃረር ኃይል መደፈቅ አለበት። ይህን ለመከወንም የዜጎችንና የሀገርን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል በህገ መንግስቱ አንቀፅ 39 መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጇል። አዋጁን የሚያስፈፅመው የኮማንድ ፖስት ሴክሬታሪያት ፅህፈት ቤት ከመሰንበቻው የአዋጁን መመሪያ ቁጥር አንድ ይፋ አድርጓል። መመሪያው የዜጎችን መረጃ የመስጠት ግዴታን

አስመልክቶ እንደገለፀው፤ ማንኛውም አካል በተጠየቀበት ጊዜ ለህግ አስከባሪ አካል መረጃ የመስጠት እንዲሁም የኮማንድ ፖስቱን ውሳኔ የማክበር እና የመተግበር ግዴታ አለበት።

ማንኛውም ሰው በኃይል፣ በዛቻና በየትኛውም መልኩ ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን የሚጥስ ተግባር መፈፀም እንደሌለበት እንዲሁም የጦር መሳሪያ ይዞ ማመፅና የእርስ በእርስ ግጭት እንዲኖር ማድረግን የሚከለክለው መመሪያ፤ የህዝቡን አንድነትና መቻቻል የሚጎዳ ተግባር መፈፀም፣ ከአሸባሪ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ማድረግና መደገፍ፣ የትራንስፖርት እንስቃሴን ማወክ፣ የህዝብ አገልግሎት ማስተጓጎል፣ ማቋረጥና መዝጋት ብሎም የመሰረት ልማት ተቋማት ላይ ጥቃት ማድረስ እንዲሁም ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን ፈፅሞ መከልከሉን ይገልፃል።

እነዚህን በመጠኑ ያነሳኋቸውን ክልከላዎች ሊፈፅም የሚችለው ማን እንደሆነ ግልፅ ነው። እርሱም ቀደም ሲል ያነሳሁትና የሁከትና የብጥብጥ አውድ ጥቂት አራማጆች ናቸው። እንዳልኩት ዛሬም ይሁን ነገ በእነዚህ ኃይሎች ላይ ከጥፋታቸው እንዲታቀቡ አሊያም በየአካባቢው ለሚገኘው የኮማንድ ፖስቱ ማዘዣዎች አሳልፎ በመስጠት እጃችንን ማውጣት አለብን።

እጃችንን የምናወጣው፤ አንድም፣ በህግ አስፈፃሚው አካል ስለተጠየቅንና ግዴታችንም ስለሆነ የህግ የበላይነት በሀገራችን ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ካለን ፍላጎት በመነሳት፤ ሁለትም፣ ለሰላማችን ዘብ መቆም ያለብን ራሳችን እንጂ የትኛውም አካል አለመሆኑን ስለምንገነዘብና ተጠቃሚዎቹም ራሳችን መሆናችንን ስለምናውቅ ነው። ርግጥም ለሰላማችንንና ለተጠቃሚነታችን ሲባል፣ ከእኛ ወዲያ ማን እጁን ከፍ አድርጎ ሊያወጣ ይችላል?—ማንም።